# በሳውዲ አረቢያ የኢትዮጵያውያን መከራ !
# የተደበቁ እውነቶች ! ክፍል አምስት

ከነቢዩ ሲራክ

## ረመዳን . . . 2003

ሐጅ ወቅት ላይ ሆኖ ስለ ረመዳንን ማውራት ሊከብድ ይችል ይሆናል፡፡ በዚህ ቀጣይ መጣጥፍ ቅኝቴ በኢትዮጵያውያን የሳውዲ አረቢያ የኑሮ ታሪክ አስከፊ የነበረውን አጋጣሚ ማዘከር ነው፡፡ ለዚህም የሆነው ሁሉ የቅርብ ምስክር ነበርኩና ከማስታወሻ ያሰፈርኩትን የተደበቁ እውነቶችን ወጋወግ ጊዜና ወቅት ሳይገድበው እያነሳሁ ብጥለው አትፍረዱብኝ ! ቀኑ ሳይታሰብ መሽቶ ይነጋል፡፡ መስከረም ሲጠባ ለጀመርኩትን ቀጣይ ወጋወግ ላስወገውግ አቅም በፈቀደ መጠን ማስታዎሻየን ሳብ እያደረግኩ በትዝታ እነጉድ ይዣለሁ ! . . . ናላን ሰብሮ የሚገባው ሃሩር ጸሃይና የቀይ ባህር ወበቅ ጭንቅ ይለቃል . . . በዛሬ ዳሰሳየ በዋነኛነት ላጫውታችሁ የምሻው በሳውዲና የመን የጠረፍ ከተማ በጀዛን ማቆያ እስር ቤት በአያያዝ ጉድለት ታጭቀው ሞቱ ስለተባሉት ወገኖች ነው፡፡ ጉዳዩን ለመከታተል እልህ አስጨራሽ ክትትል ማድረግ የግድ ቢሆንም መረጃን ማግኘቱ በዋዛ እንደማይሳካ  አላጣሁትም፡፡ እክልም ቢሆን እንደማይጠፋ ሳልገምት አልቀረሁምና ሁሉን ችየ ሞራሌን ጭምር አጠናክሬ ጉዳዩን መከታተል ከራሴ ጋር ተስማማቻለሁ፡፡ አደራ ትንፋሽዎን ሰብሰብ አድርገው ይከተሉኝ . . . እኔም ወጋወጌን ልቀጥል . . .

ወቅቱ ረመዳን በመሆኑ ቀን ላይ የጎላ እንቅስቃሴ አይስተዋልም፡፡ ለአረቦች ነዳጅ ለሰጠ ፈጣሪ ምስጋና ይግባውና የዘመኑ ቴክኖሎጂ  የወለዳቸው የተለያዩ የባውዛ መብራቶችና የሌዘር አንጸባራቂ ብርሃኖች ጂዳን አስውበዋታል ! በረመዳን ጂዳ እጹብ ድንቅ የሚታይባት ሙሽራ ናት፡፡ ሰውም ቸር ነው . . . በየመንገዱ ሲያልፍ ሲያገድም ሰላም ሳይባባል አይተላለፍም፡፡ በተለይ በጾሙ ወቅት ለአንድየ ሰላምታ አውቀዋለሁ አላውቀውም የሚባል ነገር አይሰራም፡፡ ፈገግ ብሎ በሰላምታ ከመጨባበጥ ባለፈ አብሮ እንዳደገ ትከሻ ለትከሻ ሰላምታ መለዋወጥ የተለመደ የረመዳን ወር ልዩ ውበት ነው፡፡ ቀን ላይ ሁሉም ምግብ ቤቶችና ሻሂ ቤቶች ዝግ ናቸው፡፡ ከረፋዱ ጀምሮ ቢሮዋቸውን የሚከፍቱት በአብዛኛው ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ትሥሥር ያላቸው ጽህፈት ቤቶች ፤ ለረመዳን ፍጆታ ምግብ መጠጥ ምኑ ምናምኑን የሚያቀርቡት ፋብሪካዎችና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሱቆች ብቻ ናቸው፡፡ ቀኑ ወደ ማታ የተቀየረ ይመስላል፡፡ በሌላ ጊዜ ከወጣት እስከ አዛውንቱ እዚህ እዚያ ሲጋራውን እየማገ የሚያትጎለጉለው ጪስ ረመዳን ከገባ ጀምሮ በማቆሙ አየሩ ጻዳ ያለ ይመስላል፡፡ ጾሙ ከተፈታ በኋላ ምሽት ላይ ምግብ ሲበላ እንደ ሃገራችን ሰው በቅርቡ ያለውን ይጋብዛል . . . "ፈደል"(ደ ይጥበቅ )ይሉታል . . . እባክህ እንብላ እንደማለት ነው፡፡ እንብላ ብሎ አንዱ አንዱን ሲሸማገል ማየት የተለመደ ነው፡፡ ጂዳ የምትደምቅበት ወቅት በረመዳን ሁሉም ነገር የሚሆነው ማታ ነው፡፡ ታዲያ ማታ ይህ ሁሉ ሲሆን ቀን ላይ እንዳልኳችሁ ጥድፊያ አይታይም፡፡ አውላላውን ጥርጊያ መንገድ ሞልተው የሚርመሰመሱት ሚጢጢዎችም ሆኑ ትላልቅ የቅንጦት መኪኖችም እልፎ እልፎ ውር ውር ካማለት ባለፈ ብዙ አይታዩም፡፡ ከተማዋ የተወረረች ትመስላለች፡፡ ቀን ላይ ሃይማኖቱ ምንም ይሁን ምን እንደ ሲጋራውና እንደ ምግቡ ሁሉ ውሃ መጠጣት አይፈቀድለትም፡፡ "መምኑአ" ነው ክልክል በሳውዲ ! በረመዳን ጾም የሚፈልገውን ሁሉ እቤቱ ከውኖ መውጣት ግዴታ ነው !

ነገሩ እንዲህ በመሆኑ . . . የጠዋት ቡናየን ፉት እያልኩ ማንበብ የምወደውን ጋዜጣ ረመዳን ጾም ሲመጣ ጾሙ ከተፈታ በሁዋላ ጸሃይ ካጠረዛው ወርቀት ይልቅ በድህረ ገጽ ነው ዜናውና መጣጥፍም ኮማኩሜ ወደ ምስማራበት እስማራለሁ፡፡ ረመዳን መለያየቱ መተባበሩ ጎድሎብን ለከረምን ለአብሮ አደጎች መገናኛና መሰባሰቢያ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖልናል፡፡ ለክፉ ለደጉ ብለን ካች አምና የመሰረትነው መረዳጃ ማህበር ረመዳን ከገባ ጀምሮ አርብ አርብ ምሽት ላይ በማሰባሰብ የጾም መፍቻ ፍጡር ግብዣ ማዘጋጀት ጀምሯል፡፡ ማህበሩ ጥሩ መገናኛ ስለፈጠረልን ልጆቻችንን ይዘን ከበላን ከጠጣን በኋላ የቆጥ የባጡን እየተጨዋዎትን እንለያየለንና መንፈሳችን ታድሷል፡፡ በጨዋታ መካከል አንድ ወንድሜ እንደዋዛ ጠጋ ብሎ "የሰሞኑን የአረብ ኒውስ ጋዜጣ እንዴት አየሀው ?" አለኝ ፡፡ ረመዳን ጠዋት ከማገኘው ዜና የለየኝ መሆኑን ቀልድ ቢጤ ጨማምሬ አጫውቸው እንደጨረስኩ . . . እንዴት ይህን የመሰለ ዜና አልተከታተልክም በሚል አይነት በተናደደብኝ ስሜት ጋዜጣን እንዳነብ የጀምረልኝን ወሬ ላያጠግበኝ ንክትክትት አድርጎብኝ ሄደ፡፡ ብዙም ሳልቆይ እንደዋዛ ሳልናገር ሹልክ ብየ በቅርብ ርቀት ወደሚገኝ አንድ ትልቅ ሱቅ (ሱፐር ማርኬት) አመራሁና የተባለውን ጋዜጣ አገኘኋሁ !



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

## በጅዳና ጀዛን እስር ቤቶች . . . የኛ መከራ !

የሳውዲ እውቅ ጋዜጣ አረብ ኒውስ በጀዛን ማቆያ እስር ቤት በአያያዝ ጉድለት ታጭቀው ሞቱ ስለተባሉት ወገኖች ዜና ሰፊ ዘገባ ይዞ ወጥቷል፡፡ ጋዜጣው የወጣው እለተ ሰኞ ቀኑ እንደ ፈረንጆች ዘመን አቆጣጠር ኦገስት 30 . 2010 ነው፡፡ ዜና ብቻ አልነበረም አረብ ኒውስ ያስነበበው፡፡ አንድ ታዋቂ ሳውዲ ጸሃፊም ብዕራቸውን አንስተዋል፡፡ ሰውየው በሃገሪቱ ዜጎች ዋንኛ መነጋገሪያ ርእስ የሆኑ ጉዳዮችን በድፍረት እያጋለጡ የሳውዲ ባለስልጣናት እንዲማሩበት ችግሮችን እየነቀሱ በሚያወጡበት ብዕራቸው ይታወቃሉ፡፡ ይህ መልካም ስራቸው ያስከበራቸው እውቅ ጸሃፊም ናቸውና ስማቸው ገናና ነው፡፡ አረብ ኒውስ ጋዜጣ አሁን ከሚገኝበት ነጻነት ለማድረስ ከፍተኛ መስዋዕት የከፈሉ ሃያሲም ናቸው፡፡ የጋዜጣው ዋና አዘጋጂ ካልድ አማና ይባላሉ፡፡ ካልድ የኛን መከራ የኛን በደልና ውርደት ያዘከሩበት ሰፊ መጣጥፍ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መንገድ በጋዜጣው ዋንኛ ተነባቢ ገጽ ይስተናግድ ዘንድ የከፋ ችግራችን ምክንያት ቢሆንም ለሙያቸው ያደሩ ደፋር ጋዜጠኛ ጉዳዩን ይዘውታልና መስተናገዱ የግድ ነበር፡፡ ጋዜጠኛ ካልድ በዚሁ መጣጥፍ አፍ መፍቻ ባልሆነው የእንግሊዝኛ ቋንቋቸው አሳምረው፤ ከሺነውና ቀሺረው እውነቱን ፍንትው አድርገው አሳይተውናል፡፡ እየተሰራ ያለውን ዘርግፈው አውጥተው ስሜታቸን ጨምድደውና ችግሩን አስቃኝተው በደሉ ለማንንም ዘልቆ እንዲገባ አድርገው አስነብበውናል፡፡፡ እሳቸው የሳሉትን ስዕል መሳል ይገደኛል. . . ያሉትን ፍሬ ነገር ግን በአጭሩ የገባኝን ያህል እንዲህ አድርጌ ተርጉሜዋለሁና እነሆ ፡፡ " በጀዛን የማቆያ እስር ቤት በአምስት ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመው ወንጀል ነው ፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት የጀዛን ፖሊስ አፈ ቀላጤ አብዱራህማን አል ዛህራኒ ሰወቹ የሞቱት በስር ቤቱ ባለው መጨናነቅ ነው በማለት ላሟሟታቸው የሰጡት ምክንያት ብዙወቻችን ለጉዳዩ ትኩረት እንድንሰጥበት ያደርጋል፡፡. . . ለኔ ሁኔታውን የከፋ የሚያደርግብኝ ነገር ቢኖር በተከበረው የረመዳን ቅዱስ ወር ህገወጥ ስደተኞች መሆናቸው ብቸኛ ወንጀል የሆነባቸው አምስት ኢትዮጵያውያን ለዚህ መሰሉ አሰቃቂ አደጋ መዳረጋቸው ብቻ ሳይሆን በመጨናነቅ እንደሞቱ እየታወቀ አሟሟታቸው የተፈጥሮ ሞት እንደሆነ መረጃ መቅረቡ ነው፡፡. . . ከጤና ጥበቃ ከፓስፖርት ፖሊስ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ኮሚቴ ተቋቁሞ ጉዳዩን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሞቱ የምንላቸውን ዜጎች በጉዳዩ ዙሪያ ማጣራት እየተደረገ ቢሆንም ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የሞቱትን አምስት ኢትዮጵያውያንን መልሶ በህይወት ሊያመጣልን አይችልም፡፡ ያም ሆኖ በማቆያ እስር ቤቱ ውስጥ የሚታየውን አያያዝንና አግባብነት የሌለው አስተዳደር ብዙ መሰራት እንደሚገባው ሊያመላክት የሚችል መረጃን ግን ማግኘት ይቻላል፡፡ . . . ባንድ አጋጣሚ ሹፌሬ ጠፍቶብኝ በማቆያ እስር ቤቶች ታግቶ ይሆን በሚል ለማጣራት ወደ ጂዳ ማቆያ እስር ቤት ጎራ ብየ ነበር፡፡ ያየሁት መላ አካሌን እስኪያንዘፈዝፈኝ ድረስ በመቶወች የሚጠጉ ዜጎች ንጽህናው ባልተጠበቀ ማጎሪያ እዴት ኑሮን በመከራ እንደሚገፉ ተመልክቻለሁ፡፡ ያለውን ቢሮክራሲያዊና ተቀባይነት የሌለው አሰራር ታዘብኩ፡፡ . . . እንዴት ሱኒ እስልምናን በማራመድ በቁራን በምትመራ ሃገር ይህ መሰል ድርጊት ይፈጸማል ? . . . በቪዛ በሚመጡ ነዋሪዎች በአሰሪዎቻቸው የሚደርስባቸው በደል ከዚሁ ጋር ይጠቀሳል፡፡ ሁሌም መውቀስ የሚገባን እነሱ አጠፉ እያልን ነው፡፡ እኛ ምን እየሰራ ነው ብለን ግን ማየት የቻልን አይመስለኝም፡፡ ይህ መሰሉና ተመሳሳይ የሙብት ገፈፋዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ኢኮኖሚዋ እያደገና በጥሩ ጥሩ ምግባር ስሟ እየታወቀ የመጣውን የሃገራችንን መልክ የሚያበላሽ በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግበትና ሊቆም ይገባል፡፡ በሚሊዮን ለሚቆጠሩት የውጭ ዜጎች ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ መልካምነታችንን እንዴት ሊያወሩ ይችላሉ ብለን እራሳችን እንጠይቅ? መልካም ስራችን እንጅ ሰብ አዊ ሙብት አክባሪነታችን በጥሩ ምሳሌነት ሊታወቅ ይገባልና በዚህ ረገድ ብዙ መሰራ አለበት ፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትነው አይነትም ሆነ ተመሳሳይ የሙብት ረገጣን የሚጠየቁ አካላት ፍርድ ማግኘት አለባቸው፡፡ ከላይ ያነሳሁት የኢትዮጵያኑም አሟሟት ተጣርቶ ጥፋተኞች ቅጣት ሊሰጣቸው ይገባል! " በማለት የተባ ብዕራቸውን በግፉአኑ ላይ ለተሰራው ወንጀል ፍትህ ይሰጥበት ዘንድ ለሚመለከታቸው ሁሉ በአደባባይ አቤት ብለዋል፡፡ . . . " በዜጎቻችን ላይ እየሆነ ያለውን በቅርብ ለሰማን፤ ላየንና ለምንከታተል እውነታው በታዋቂው ጋዜጠኛ ፋና ወጊ መጣጥፍ ይፋ መሆን ከደስታ ፌስታ ባለፈ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡ በዚህ አጋጣሚ ብዙዎች የመደሰታችንን ያህል ሃቁን ለመቀበል የፖለቲካ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ እውነቱን አንሸዋረን የምናይ ወገኖች ሃቁን ለመቀበል ስንቸገር የተስተዋለበት አጋጣሚ ተስተውሏዋል፡፡ በተጓዳኝ በማውቅና ባለማዎቅ ሃላፊነታቸውንና ተጠያቂነታቸውን አሽቀንጥረው ጥለው ግፉ ሲፈጸብን ተመልካች ለሆኑት ተወካዮቻችን ይህን መሰሉ አንገብጋቢ መጣጥፍም ይሁን ይህ መሰሉ ዜና ይፋ መሆን አንገታቸውን የሚያስደፋ አሳዛኝ አጋጣሚ እንደነበርም የታሪክ ምስክሮች ሆነናል፡፡ በጋዜጣው የተጠቆሙት የሙብት ረገጣወች ገሃድ መውጣት አሚሮች ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡት ብቸኛ መፍትሄ ነው ብለን ለምናስብ ወገኖች



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

ድቅድቁን ጨለማ በመሰንጠቅ ሾልካ ውስጥ ለውስጥ የገባችን ብርሃን ትንሽየ ተስፋ ሰጥቶናል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ለወራት ስናነሳ ስንጥልው የከረምነውን ጉዳይ ጋዜጣው ከነመረጃው እየተጣቀሰ መቅረቡ የድካም ዋጋን እንደማግኘት ያህል ይቆጠራልና ይህንንም ስሜቱን መግለጽ ይከብዳል ! የመንግስት ሃላፊዎችቻችን ምን እየተሰራ ነው ? እዚህ እዚያ ጪኸት በርትቷል ? መፍትሄውስ ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ "የተቃዋሚዎች እጇ አለበት ፤ ገጽታችን ለማጥፋት የሚደረግ ቅስቀሳ ነው. . . ወዘተ " እየተባልን አሳር መከራቸን ለበዛ ወገኖች ሌላው ቢቀር እውነቱ ወጥቷልና የህሊና እረፍት ሰጥቶናል ! እሰየው ነው !

## ብልጭ ያለው አዲስ ተስፋና አሰቃቂው መርዶ . . .

የሰብአዊ መብት መስሪያ ቤቶች አለ የተባለውን ችግር እያነፈነፉ በመሄድ በማይንቀሳቀስና በተንቀሳቃሺ ምስል (በቪዲዮ) ማንሳት ያዙ፡፡ መረጃ ለማሰባሰብ ሁኔታወች መጠናቀቃቸውን ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ ለከፍተኛ የሃገሪቱ መሪዎች ጠረጴዛ ለውሳኔ መቅረቡን "አልተናገርንምም. . . አልሰማህም" ብለው መረጃ አሾልከው ያቀበሉኝ ወገኖች የስማቸውን መጠቀስ ቀርቶ መረጃ ከነሱ ስለመውጣቱ እንዳይታወቅ በበማስጠንቀቅ ያህል አሳሰቡኝ፡፡ ይህን መሰል መረጃ በይፋ ለመስጠት ለምን እንዳልፈለጉ አውጠነጠንኩ፡፡ ያለሁበትን አካባቢ ላፍታም የዘነጋሁ አይመስልም ትላላችሁ? . . . ብቻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገሪቱ እየታየ ያለ ለውጥ ቢኖርም አዳጊ ተመንዳጊው ግልገል ነጻነት አደጋ አይጠፋበትምና መፍራታቸው ብዙም ሊያስደንቅ አይገባም ! አልኩና ዝምታን መርጨ በተሰጠኝ ተስፋ ተጽናንቸ ተመለስኩ፡፡ በዛሬ ውሎየ ያገኘሁት ተስፋ ለተሙዋጠጠባቸው ወንድሞች ሰላም እንደሚሰጣቸው ተረድቻለሁ፡፡ የምጠብቀው የተለመደው የስልክ ጥሪ MISS CALL እስኪደርሰኝ ነው፡፡ ተስፋ የሆነኝን መረጃ ሹክ ለማለት ተጣደፍኩ፡፡ ሰአቱ ደርሶ ተደወለልኝና በደስታ ተሞልቸ የሰማሁትን አሰማለሁ ስል መስማት የማልፈልገው መርዶ ከታሳሪ ወንድሞቸ ሰማሁ፡፡ በበርሃው ንዳድ እየተሰቃየ ታሞ ተቸግሮ ውሎ አዳሩን ያጫውተኝ ወንድም ሳይደላው ሳይመቸው ቀዝቃዛ ውሃ ሳያገኝ ሃገሬ ልግባ እንዳለ ነብሱ ከስጋው ተለየች ! "ጠዋሪ ለሌላት እናቴ ተስፋ ልሁናት" ሲል ተስፋው እንደ ቀቢጸ ተስፋ ሆኖ አረፈው ! ጠምዶ አርሶ ወንድም እህቶቹን ይደግፍ የነበረው ወንድም ከሚወዳቸው ቤተሰቦቹና ከቀየውና ከዚህ ውጥንቅጥ አለም ማለፍ ሳይችል ቀረና ህይወቱ በጻእር አለፈች . . .ሞተ አሉኝ ! ዛሬ ድምጹን እንጂ እሱን አላገኘውም ! ነገን በተስፋ እንዲኖራት መጽናኛ የሚሆን መረጃ ላበስረው ስጓጓ ወንድሜ አመለጠኝ ! . . . በቃ ተሰናበተ ! በጂዳ ቆንስል መስሪያ ቤት በማቆያ እስር ቤት ያሉትን ዜጎች የሚከታተሉት ወንድሞቸ ማለዳ ላይ ሬሳው ጅምባ ጅንቦ ብለው ማውጣታቸውን ሰማሁ፡፡ ይህ በረመዳን 15 ቀን ውስጥ የወጣ 6ኛ ሬሳ መሆኑንም ከታሳሪዎች ሳይሆን ከቆንስል መስሪያ ቤቱ ታማኝ ምንጮች ያገኘሁት መረጃ ይጠቁማል፡፡ ይህ ድርሰት አይምሰላችሁ ! አዎ . . . ዛሬ የማወራችሁ የትናንቱን መከራ እያስታወስኩ እንደሁ አትዘንጉ፡፡ በማስታወሻየ ጽፌ የያዝኩት አብሮኝ የሚኖር የማልረሳው ትዝታ ነውና ! . . . ልብን ዘልቆ የሚያደማ ደረቅ የተደበቀ እውነት ነው ! በእርግጥ ችግሩ የተቀረፈው ልክ ከዛሬ አንድ ወር ታሳሪዎች ይህ ምሬት ፈንቅሎዋቸው እስር ቤት በሰበሩ ማግስት እንጂ በሃገራቸው በዲፕሎማቶቻችን ትረት እንዳልነበር አፉችን ሞልተን መናገር እንቻለን ! ለመብታችው መከራከር ቀርቶ ለወራት እንግልታቸው ያልተጠናውን የዜግነት ማጣራት አዲስ ፖሊሲ ሲዎርድ እንደማይሆን እያወቁት መቃወሙና የሚሆነውን መናገሩ ወንበራቸውን የሚያንቀሳቅስ ስለመሰላቸው ዝምታን መመረጡን በሹክሹክታ ይሰማ እንጂ ሃቅ ያለው እውነት መሆኑን መናገር ይቻላል፡፡ በዚህ ሰበብ ለተፈጠረውን አይነት ግፍ በዚህች ሃገር በማናቸው ዜጎች ሲሰራ አልሰማንም አላየነም ፡፡ አሁን ሁኔታወች ተቀያይረዋል፡፡ ለዚህ ሁሉ መተረማመስ ምክንያት የሆነው የዜግነት ማጣራት በመርገቡና የኛ መንግስት ዲፕሎማቶች ከአምስት ወር በኋላ በከፍተኛ ጉትጎታ ማጣራቱ በመቀላጠፍ ችግሩ ለመፈታት መጀመራቸው ያስደስታል፡፡ ከወራት በኋላም ዲፕሎማቶች ታሳሪዎችን ጎብኝተዋል፡፡ ይህም ቀጣይነት ቢኖረው ወሸኔ ነው፡፡ ያም ሆኖ እንደኔ አይነት የነሱ "ምቀኛ" እስከዛሬ የት ነበሩ ? በሚል የሚያነሳው ጥያቄ መልስ አላገኘም . . . መልሱንም ሆነ ተጨማሪ መረጃውን ከዚህ ሁሉ መከራና ሰቆቃ የተረፉት ዛሬ ሀገር ቤት ገብተዋልና የምስክርነት ቃላቸው መናገር ከቻሉ እንሰማዋለን፡፡ ተናግረው ከችግሩ ሊያስተምሩን ብቅ ብቅ ሲሉ ነገ ተነገ ወዲያ ላጭ በሚዲያ አለያም የመንደር ወሬ ሆኖ ሳንሰማው አይቀርም፡፡ National Society for Human Rights ተብሎ የሚጠራው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ቡድን የጂዳና መካ ሙከረማ ዳይሬክተር ዶ/ር ሁሴን አልሽሪፍ በጂዳ ማቆያ እስር ቤት መጎብኘታቸው ተከትሎ በእስር ቤት አካባቢም የህክምና ሁኔታው ከወትሮው በተለየ መንገድ መሻሻል ማሳየቱን ታሳሪ ወዳጆቸ አጫወቱኝ፡፡ ከአንድም ሁለት እስረኞች በእስር በሚገኙበት ሁኔታ መሞታቸው በተለይም በሴቶች እስር ቤት የአንዲት የ 4 አመት ህጻን ልጅ መሞትና የአንዲት ነብሰ ጡር በእስር ላይ ምጥ



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

ይዟት ልጇን በመገላገል ላይ እንዳለች መሞትና ተመሳሳይ ችግሮች ታሳሪዎችን አስቆጣ፡፡ ከጭንቀትና ከብስጭት የተነሳ በር እየደበደቡ የሃላፊዎችን ትኩረት መሳብ ቻሉ፡፡ ተጨማሪ የወታደር ሃይል ቢመጣም ሁኔታው ሊበርድ አልቻለም፡፡ አንድ ምሺት ላይ ረብሻው ጠነከረና የእስር ቤቱ ሃላፊዎች ሌሊት ላይ ከየቤታቸው ተፈልገው መጡ፡፡ ታሳሪዎችን በተወካይ አማካኝነት ለማነጋገር እንደሚፈልጉ አስታወቁና ታሳሪዎች ይወክሉናል ያሏቸውን ተወካዮች ከተለያዩ ማሰሪያ ክፍሎች መርጠው ላኩ፡፡ ኢትዮጵያውያን ታሳሪዎች ከጀኔራሉ ቢሮ በችግራቸው ዙሪያ ውይይት አደረጉ፡፡ ታሳሪዎችን ያነጋገሩት ጀኔራል የታሳሪዎች ለወራት መንገላታት ምክንያቱ የቆንስል መስሪያ ቤቱ የመጓጓዣ ሰነድ አለማቅረብ እንደሆነ ገልጸው አስፈላጊ ከሆነ ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ አሁን ድረስ ሂደን እናሳያችሁ በማለት የአንድ ዲፕሎማትና የጉዳይ ፈጻሚውን ተንቀሳቃሺ ስልኮች ደወለው ስልኮቹ ዝግ እንደሆኑባቸው ያጫወተኝ ተወክሎ ከሄዱት ታሳሪዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ትክክለኛውን እውነታ በመግለጽ ታሳሪዎችን ማረጋጋት ተቻለ፡፡ ጩኸቱም በረደ ! አሁን ችግሩ በትክክል የት እንዳለ ታወቀ ! ይህም "የዜግነት ማጣራት" በሚል ፓስፖርትና ሊሴ ፓሴ (የመተላለፊያ ወረቀት) ወደ አዲስ አበባ ለማጣራት መሄድ መጀመሩ ለወራት እንግልት እንደዳረጋቸው ከእስረኞች አልፎ እኔ ዳር ዳሩን ስሄድ ላገኘኋቸው መረጃዎች ማረጋገጫ ሆነ ! ያ ሆኖ ይህንን የሚያጠናክር ሌላ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሙከራየን ቀጥያለሁ . . .

## "የላሜ ቦራ" ጩኸትና ያልበራልን " የዲያስፖራ" ሻማ . .

ይህንን መጣጥፍ ወደናንተው ለማቅረብ ስንገታገት ላንዳፍታ አዲስ ዜና ካለ በሚል ከመካከሉ በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ በቢጫ ኮከብ ያረፈበትን ያምናና የቅርብ አመታት የኢትዮጵያውያን መለያ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዴራ ይልቅ ኮከብ በሌለባት በቀድሞዋን የኢትዮጵያ ባንዴራ ያሸበረቁ የኢትዮጵያውያን ድህረ ገጾችን አዲስ ነገር ካለ በሚል ስመለከት አንድ የሻማ ማብራት ጥሪ ቀልቤን ሳበው፡፡ የወጣቱ ኢትዮጵያዊ አሊ አህመድ ዲሲ 9 በመባል በሚታወቀው ክለብ ባለቤትና በአምስት ጠባቂዎቻቸው(ቦዲጋርዶች) ጭካኔያዊ በተሞላበት ሁኔታ ተደብድቦ በግፍ በመገደሉን በምድረ አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተቃውሞዋቸውን አጠናክረው በማሰማት ላይ መሆናቸውን ተረዳሁ፡፡ ገዳዮች ፍርድ ቤት ቀርበው በዋስ መለቀቃቸውና የተከሰሱበትም የግድያ ወንጀል አይነት ዝቅ እንዲል መደረጉ ፍርዱ "ፍርደ ገምድል" እንደሆነ በመቃወም ለሙዋች ዓሊ አህመድ ቤተሰቦች "አለንላችሁ" ለማለት ከጎናቸው መቆምን ለማሳትየት ማክሰኞ– Oct 19, 2010 የሻማ ማብራት በርካታ በዋሽንግተን አካባቢ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተሳታፊ በመሆን ግፍን ተቃውመው ለፍትህ ጥያቄ መቆማቸው አስቀናኝ ፡፡ ይህ ዜና እያነሰን ከምንጥለው የአረብ ሃገር ስደተኞች ጉዳይ በንፅፅር እንዳየው ውስጤን አንዳች ነገር ገፋፋኝ፡፡ የኢትዮጵያውያኑ ድህረ ገጾች በሰፊው መናኘት ከጀመሩባቸው ካለፉት ሰባትና ስምንት አመታት ወዲህ የተለየ ዜና ስላለማየቴ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ያም ሆኖ ዛሬ መረጃዎቹን የማያቸው እንደቀድሞው አይደለም፡፡ ዲሞክራሲ መብትና ነጻነት በጥቂቱም ቢሆን ይገባቸውዋል ተብሎ ከሚታመኑት ዜጎች መካከል በሰለጠነው አለም የሚኖሩ ስደተኞች መሆናቸውን ሙሉ በሙሉ ባልስማማም የማምንበር ነጥብ ግን አይጠፋም፡፡ የቡድን ቀርቶ በግለሰብ ላይ የሚሰነዘርን የመብት ገፈፋ በጽኑ እየተቃዎሙ ድምጻቸውን ማሰማታቸው የምስማማበትና መሆን አለበት ብየ አምናለሁ፡፡ በዚህ ረገድ በርካታ መረጃወችን የተመለከተ ማንነቴ ለግለሰብ መብት ጥብቅና የቆመው በውጭ የሚኖረው ማህበረሰብ  በአረብ ሃገራት ስደት የሰቆቃ ኑሮን የሚገፉ ወገነኖችን ጉዳይ ግን አንድም ቀን አንስቶ ሲናገር አልሰማሁም፡፡ ይህ ለምን ሆነ አልልም፡፡ ይህ ያልሆነበትን ግራ ያጋባኝ ከያዘ ቢከራርምም መልስ ለዚህ መልስ አጥቸለት ከርሜያለሁና አሁን ሌላው ቢቀር ለራሴ ሁኔቱ በጸጋ የምቀበለው አልሆነምና ምክንያቶችን ለራሴው ደርድሬ ልዩነቱ ማየት ያዝኩ. . . አሁንም ራሴን ለማሸነፍ ! ቀጥልኩና በሃገረ አሜሪካ ተደብድቦ ተገደለ ስለተባለው ኢትዮጵያዊ በሁኔታው አዝኘ፤ ነብሱን ይማር አልኩና ወደ ራሴው ሃሳብ ተመልስኩ ! በአሜሪካ ተገደለ የተባለውን ኢትዮጵያዊ ወንድምና ከላይ በእስር ላይ እንዳሉ በመጨናነቅ ሞቱ የሚል ማረጋገጫ የተሰጠባቸውን ኢትዮጵያዊነት ሚዛን ላይ አስቀመጥኩት፡፡ በደምሳሳው ለምናየው ለኛ ልዩነቱ አይታይም . . . ከሞቱት ቁጥር ባለፈ በግርድፉ እንኳ በሰባዕና ብናየው በትክክል ልዩነት አለው . . . ይህ ለኔና መሰሎቸ ነው ! ልዩነቱ ከመንግስት ከተቃዋሚዎች ይጀምርና ወደ ነዋሪው መድረሱንም መካድ አይቻልም . . መንግስት ጉዳዩን በፓርላማ እንስቶ ሃቀኛ ክርክር አያደርግም፡፡ ልዩነቱ የዜጎችን ችግር ተመልክቶ እውቀቱ ያላቸው በቂ ዲፕሎማቶችን በተገቢው ቦታው ማሰማራት ካለመቻሉ ይነሳና ልዩነቱ ደረጃውን ጠብቆ ይወርዳል፡፡



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

በአንጻሩ ለኢትዮጵያውያን እኩል መብት ቆመናል የሚሉት የተቃዋሚ ፖለቲከኞች የአረብ ሃገር ኢትዮጵያውያንን ችግር ለፓለቲካ ፍጆታ በሚመስል መልኩ እንጂ ጉዳዩን አለም ሰምቶ አንድ እንዲለው ድምጻቸውን ከፍ አድረገው ማንሳቱንም ሆነ ቁራጭ ሻማ አብርተው በደሉ ፍርድ ይሰጠው ዘንድ ድምጻቸውን ሲያሰሙ አይስተዋልም፡፡ አሁንም ወደ ዝርዝሩ አንገባም ! ልዩነት ስላልኩት የገባኝን ያህል ትረዱልኝ ዘንድ ሁሉንም ትቸ አሜሪካ ሞተ ስለተባለው ወንድምና በጅዛን መሞታቸው ስለተነገረን ወንድሞች አሟሟት እንመልከት፡፡ በምሳሌነት የማጣቅሰው በሃገረ አሜሪካ ለተሰራው ወንጀል ገዳዮች ፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ ፍርድ ግን ተዛባ መባሉ ተቃውሞ አስነስቷል፡፡ በንጽጽር በሳውዲ ሞቱ እየተባለ ለሚነገረን ስደተኞች ኢትዮጵያውያን "በአያያዝ ጉድለት" ሞቱ ተብሎ በራሳቸው መገናኛ ብዙሃን መረጃ መሰጠቱ እውነት ነው. . . ዲፕሎማቶች ግን ይህን አጋጣሚ ወደ ፍርድ ለማቅረብ ቀርቶ ወሬው የተናገረ "እርጉም ከመአርዮስ" ማለታቸውን ገፍተውበታል ! በሰለጠነው ሃገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የአንድነት ፖለቲካ ፓርቲ መሪ የሆኑት ወ/ት ብርቱካን ከእስር እንዲፈቱ በርካታ የሻማ መብራት ስነ ስርአቶች አድርገዋል፡፡ በሃገር ቤትና በውጭ ሃገራት ፍትህ ሳያገኙ ለሞቱት ፤ ለተደበደቡት ፤ ለታሰሩትና መብታቸው ላልተጠበቀላቸው ታዋቂ ግለሰቦች ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሰባዊ መብት ጥብቅና የሚቆሙ ኢትዮጵያውያን አለም ችግሩን እንዲሰማው ሻማ ሳያበሩ ድጊቱን በተባ ብዕራቸው ሲገልጹ የቀረቡበትን አጋጣሚ አላስታውስም፡፡ ለሚጉዋደለው ፍትህ ለሚጠፋው ኢትዮጵያዊ ብዕር ማንሳት ይቅርና በነጻዎቹ በአውሮፓና በአሜሪካ አደባባዮች አንድም ቀን አንዲትም ሻማና ሲበራ አላየሁም ! ምክንያቱ አሁን ድረስ ባይገባኝም ሻማ ተወዶ እንዳልሆነ እግጠኛ ነኝ !

ያን ሰሞን ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ሃገር ቤት ጎራ ብየ ካንድ ለመረጃ ቅርብ ከሆነ ወንድሜ ጋር ስናወጋ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ቀልድ ሰማሁ፡፡ ናፍቆኝ የከረመውን ጃንቦ ቢራ ጋር እየተጎነጨሁ ካንድ ወንሜ ጋር በሚሊኒየም መባቻ እየገነነ ስለመጣው በውጭ የሚኖሮ ኢትዮጵያውያን ቅጽል ስም ዙሪያ ሲወጣ የአረብ ሀገር ስደተኞች "ላሜ ቦራ" የአውሮፓና የአሜሪካ ስደተኞች ደግሞ "ዲያስፖራ" መባላቸውን ሰምቻለሁ፡፡ "ላሜ ቦራ" ማለት ምንድነው አልኩ፡፡ የአረብ ሃገሩ ስደተኛ ባሳር በመከራም ቢሆን ሰርቶ ወገን ቤተሰቡን የሚደግፍ ስለሆነ ነው አለኝ ወንድሜ ! በእርግጥም የአረብ ሃገሩን ነዋሪ ሃበሻ የተሰጠው ስም ተጠንቶ እንጂ እብድ ከመንገድ የለጠፈበት ስም አይመስልም፡፡ ላሜ ቦራ ጠዋትና ማታ እየታለበች ወተቷን በመስጠት ባለቤቷቾን መደገፉዋ እውነት ያለው ሃቅ ነው፡፡ "ላሜ ቢራ" እንደ "ዲያስፖራ" የደላት የተመቻት ብቻም ሳይሆን መሰረታዊ መብቷ የተከበረ ስላለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ "ላሜ ቦራ" በዘመናዊው ባርነት ተደፍቃ ያላትን ለቤተሰቡዋ እየላከች ትደግፋላች ፡፡ ጩኸቷን የሚያስተጋባላት ግን አድሎ ይደረግባታል፡፡ ደጋግሜ እንዳልኩት "ላሜ ቦራ" የተረሳች ትመስላላች ! . . . እንደ "ዲያስፖራ" ስትቸገር ሻማ የሚለኩስላት እንኳ የለም ! ለምን ይህ ሆነ ብሎና ችግሩ ምንድን ነው ብሎ መጠየቁ ደግ ቢሆንም መልስ የለኝም ?

## ተንከራታቾ የኛ ከበሮ ደላቂ እህት . . .

በክፍል አራት መጣጥፌ ለንባብ በበቃ ማግስት ጠዋት ላይ ወደ ድልድዩ ስር ጎራ ብየ ነበር ፡፡ ያች በክፍል አራት ያወጋኋችሁ እህት ለወራት ተጠልላ ከበሮ ትደልቅበት ከከበረችው ድልድይ ስል የለችም፡፡ በዙያ ገቡ መኪና በማጠብ ከሚተዳደሩት የሶማሊያውያንና ጥቂት የህንድ የፓኪስታን የሲሪላንካና የኢንዶኖያ ዜጎች ብቻ ይስተዋላሉ፡፡ ሲደከማትና ሲታከታት ጋደም የምትልባት የድልድይ ታዛ ባዶ ሆናለች ፡፡ ያ ቦታ ድንጋይ ተደርድሮበት የካርቶንና ቁርጥራጭና ወዝ የጠገቡና ብጥስጣሽ ጨርቃ ጨርቆች ብቻ እዚህም እዚያም ይታያል፡፡ እሱዋ ግን የለችም ! በአካባቢው የሚገኙ መኪና የሚያጥቡ ሶማሌዎችን ጠየቅኩ፡፡ እሱዋኑ እያሰቡ ጸዳ ብሎ የለበሰ ሃበሻ ሲያዩ ይበሳጫሉ፡፡ እኛስ አገር መንግስት አልባ ነን እናንተ ምን ሆንችሁና ይህችህ ምስኪን ረሳችሁዋት ? ብለው መጠየቃቸው ባይቀርም መልስ የለኝምና አድበስብሸ ማለፍ ነበረብኝና ይህንኑ አደረግኩ፡፡ ጠዋት ሲመጡ እንዳላገኙዋት ገለጹልኝ. . . የለችም አሉ ! ምናልባት ድምጻችን ተሰምቶ መልስ አግኝታ ይሆን ስል ራሴን ጠየቅኩ፡፡ ወደ ኢንባሲው የችግር አስወጋጂ ኮሚቴ በህዝብ ገንዘብ ወዳሰራው መጠለያ ተወስዳ ይሆን በሚል ወደ ጂዳ ቆንስልም አመራሁ፡፡ እዚያም የለችም. . .ፍሊጋየን ግን አላቆምኩም፡፡



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

## አዲስ ዲፕሎማት . . . አዲስ ተስፋ ! እንበል ይሆን ?

የአረብ ሃገሩን የስደት መከራ ታሪክ ላኮበኮቡ ኮበሎችና ጉብል እህቶቻችን ማስተማሪያና ሁኔታውን ላላወቁት ለማሳወቅ የሚሰጠው ፋይዳ ቀላል አይሆንም የሚል ጽኑ እምነት ካደረብኝ ከራርሟል፡፡ መሞትን እያወቁ መኖር እኮ ከፈጣሪ ጋር የመታረቅ ያህል ነው ጎበዝ ! እናም ተሚጦ የቀረው ብቸኛው አማራጭ ላላዎቁት ማሳዎቅ አይደለም ትላላችሁ? ጉዳዩን በአግባቡና በቅንነት መመልከት ለቻልን እንደኔ እንደኔ የዚህ እውነታ አንድምታው ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ ሌላው ሁሉ ይቅር እንበል. . . የትናንቱን ዛሬ ስበን እያመጣን ማዘከራችን የሚቆረቆርልን የመንግስት ተዎካይ እንዲሾምልን አደራ ለማለትስ አይሆንም ትላላችሁ ? ደግሞም ከዘንድሮው ምርጫ በኋላ አዲሱ መንግስት በመተካካቱ ገፍቶበት በ17 አመቱ ተጋድሎ ጥይት ያልተኮሱ አዳዲስ ሹሞች ብቅ ባሉ ማግስት ለኛም አዳዲስ ዲፕሎማቶች ተሹሟል፡፡ በጅዳና በአካባቢው በከፍተኛ ሃላፊነት ያገለገሉት አምባሳደራችን ታህሳስ አልፎ ጥር ሲጠባ 15 አመታት በቆንስላነት ያገለገሉበትን የሞቀ ወንበር እንደሚለቁ እርግጠኛ የተባሉ መረጃወች መገኘት ጀምረዋል፡፡ በመከራ ኑሮን ከሚገፉት ነዋሪዎች መካከል አንዱ ነኝና እንደተቀረው ወገኔ "ማን ይሾምብን ይሆን" ማለቴ አልቀረም፡፡ ዘንድሮ የሚሆነው አይታወቅምና የሚመጡልን እንበለው የሚመጡብን ሃላፊዎች የአሜሪካው መሪ ኦባማ ስልጣን ሲረከቡ እንዳሉት ካለፈው ለመማር መስማት እዝነ ህሊናቸውን ከፍተው ከሰሙን ለችግሮች መፍትሄ ማግኘት ይቻላል የሚሉ የትየለሌ ናቸው ፡፡ ለጂዳው ግፉአን የቆዩ ታጋይ፤ አዲስ ታጋይ ፤ በመተካካት የመጡ መሆናቸው ችግር አይደለም ! ብቻ እዝነ ልቦናቸውን ወደ ነዋሪው እንጂ ወደ ወሬ አቀባይ ካድሬዎች እንዳያደርጉ ግን የዛሬ ጸሎታችን ሆኗል ! አሮጌውን ትዝታ ለታሪክ እያዘከርን በአዲስ ዲፕሎማት አዲስ ተስፋ የምናይበትን ቀን ለማግኘት ብቸኛው ዘመንኛ መፍትሄ ችግር የሚፈታው በመደማመጥና መነጋገር ነውና ለዚሁ የሰለጠነ መንገድ እንዲያደርሰን በጸሎት እንትጋ ! አዲስ ዲፕሎማት አዲስ ተስፋ እንበል ይሆን ? ጥሩ መመኘት ጥሩ ነው !

## የመጨረሻዋ ሰዓት መልካም ዜና . . .

ያንድ ዘምን የጀርመኖች ዋና ከተማ ነበረች የሚሏትን ስመ ገናና ግን ጠበብ ያለች ከተማ ቦንን በወፍ በረራ ቅኝት ለማየትና ስልጠና ቢጤ ለማድረግ የምገኘው እዚያው ነው፡፡ ብርዱ ምንቴስ ያሳቅፋል የሚሉት አይነት ነው፡፡ "እጂግ ቀዝቃዛው የክረምት ወር እየተቃረበ መምጣቱን ጠቋሚ እንጂ ዋናው ክረምት እንዲህ አይደለም" ያለኝ ከፍራንክፈርት አየር መንገድ ወደ ቦን ያደረሰኝ ቶማስ የተባለ ጀርመናዊ ወጣት ነበር፡፡ ከሃሩርና ከንዳድ ለመጣሁት ቀርቶ ብርዱ ለቶማስ ከብዶት ካደረገው ካፖርት በተጨማሪ አንገቱን በእራፊ ሱፍ ጨርቅ ጠምጥሞ ራሱን ያሟሙቃል፡፡ በሁለተኛው አለም ጦርነት ወቅት እንደተሰሩ የሚነገርላቸው የቦን ዘመን ጠገብ የቆዩ ህንጻዎችና በራይን (ስሙን ገና አስተካክየ መናገር አልቻልኩም ከሆነ መሰል ይቅርታ) የራይን ወንዝ ለቦን ውበት እንደሰጡዋት በድህረ ገጽ የሳተላይት ፎቶዎች ያየሁትን ዛሬ ወደ ሆቴል ስጓዝ ቶማስ አሳይቶኛል፡፡ የስደተኛ ወንድምና እህቶቻቸው ድምጽ እንዲሰማ ትልቁን ስራ የሰሩትን የስራ ባልደረቦቸን በአይነ ስጋ ለመገናኘት ጉዋጉቻለሁ፡፡ የረዥም ጊዜ የሪፖርተርነት ህይዎቱ ከበታች ጋዜጠኞች ጋር እንዴት ማደር እንዳለበት ጠንቅቆ የሚያው የሚመስለኝ ጀርመናዊ አለቃየና ትጉህ ኢትዮጵውያን ጋዜጠኞች እኔንና የተቀረነውን እንግዶች በስልክና በአካል በመገኘት ሞቅና ደመቅ ባለ የእንኳን ደህና መጣችሁ ሰላምታ ተቀበሉን፡፡ እኔ ከአረብ ሃገርና የቀሩት ከተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት ለመጣን ጋዜጠኞች ሞቅና ደመቅ ያለው አቀባበል በሰማይ ጠያራው በረራ የደከም ሰውነታችን በትፍስህት ዘና አደረጎታል ! ከአስመራ ካይሮ ከካይሮ ፍራንክፈርትና ቦን ጀርመን ቀኑን ሙሉ በረዝሙ በረራ ሲንከራተት የዋለው ጎይቶም ቢሆን የቦን ጭጋጋማ ሰማይ ደንገዝገዝ ሲል በሆቴሉ ደረሰ፡፡ በድምጽ እንጂ በአካል ከማላውቀው ባልደረባየ ጋር ተገናኘን፡፡ ትንሺ ካረፈ በኋላ ምሺት ላይ የማይጠገበውን የጋዜጠኛ ጎይቶም የቆየ ትዝታ መኮምኮም ከተሰማኝ ልዩ ነጻነት ጋር የመታደልን ያህል ነበር ! ጎይቶም ቦታ ፤ ስም ፤ ድርጊት ከነሰአቱ ምንም ያህል ዘመኑ ቢለጠጥ አይረሳውም ፡፡ ያም ሆኖ አንዳንዴ በጨዋታ መካከል ስም ሲጠፋው ተስረቅራቂ ሳቁ ይቀድመውና " አንተየ አረጀሁ መሰል?" እያለ አንገቱ በትህትና ዘውር እያደረገ የሚያመጣው ጨዋታ እያሟሟቀኝ ብርዱን አስረስቶኛል፡፡ . . . ከጎይቶም ጋር ተለያይተን ወደ የመኝታ ክፍላችን እንዳመራን ከሳውዲ የደረሰኝ የስልክ ጥሪ ነበር ፡፡ የዚያችን ልጅ ነገር አደራ? ሌላው ቢቀር መዳረሻዋን . . . ያልኩት ወንድም የመገኘቷን ብስራት አቤረኝ ! . . . እየበላሁ እየጠጣሁ ሆዴን ይርበው ነበርና የጎደለው ነገር ተገኘ መሰል አሁን ሆዴ ሞልቷል ! ሞቅ ያለው ምሺት ሞቅ ባለ የምስራች ወሬ ደምቆልኛል ! ዛሬን በዚህ ልሰናበት ! ከሃገረ ጀርመን ሆኘም ቢሆን ያንን ቀን ማዘከሬን ግን እቀጥላለሁ ! የተደበቁ እውነቶች ቅኝቴ ገና አላበቃም . . .

ቸር ይግጠመን ! ህዳር 2003 ዓ.ም / ቦን- ጀርመን



This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com